# የኢትዮጵያችን መለያ የሆነው የፊደል ቅርስነት

ሓጎስ ኣረጋይ (PhD) መስከረም 9፣ 2010

እንደ ኣሁኑ ኣይሁንና ኢትዮጵያ በስልጣኔ ማማ ላይ እንደነበረች የሚያበስሩን ብዙ ዓሸራዎች እንዳሉ ይታወቃል። ከብዙዎቹ ዓሸራዎች መከከል ድምፅን ሊወክል የሚችልና እስከ ኣሁንም የዘለቀ የራሳችን የፊደል ባለቤት መሆናችን ለነበረን ስልጣኔ ማሳያ ነው የሚል እምነት ኣለኝ ። ምክንያቱም በዚያን ወቅት ድምፅን ሊወክል የሚችል ፊደል መቅረፅ መቻል ማለት በስልጣኔ ማማ ላይ መኖራችን የሚያሳይ ጉልህ ምሳሌ ነው ብንል ማጋነን ኣይሆንም። ነገር ግን ፣

**የፊደለቹ መነሻ የትና እንዴት ይሆን ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ሊሆን የሚችለው በኣክሱም ዘመነ መንግስት በድንጋይ ላይ ተፅፈው ከሚገኙት ምልክቶች መካከል እንደ "ሐ"፣ "ረ" እና የመሰሳሉት ኣሁን ላሉ ፊደሎች በመነሻነት ሊያገለግሉ ይችላሉ ብለን ልንወስድ እንችላለን ።**

ስለዚህ በኣሁኑ ሰዓት በግእዝ፣ በኣማርኛ፣ በትግርኛ ወዘተ የምንጠቀምባቸው ፊደሎች ከኣክሱም ስልጣኔ ጋር እያደጉና መልክ እየያዙ የመጡ መሆናቸውን ሁላችንም ሊያግባባን የሚችል ሃሳብ ይመስለኛል። በተመሳሳይ መልኩም እኔ ራሴ የኣክሱምን ሙዝየም በጎበኘሁበት ወቅት፣ የሙዝየሙ ባልደረባ የገለፁልኝ ከላይ ያስቀመጥኩት መላምት ነው። በእርግጥ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ኣለ፣

**ኣንዳንድ ወገኖች ግእዝን ከቋንቋ መሳርያነቱ ባሻገር በቀጥታ ከሃይማኖት ጋር የሚያቆራኙ ሊኖሩ ይችላሉ። እውነታው ግን የተኛውም ቋንቋ ተጠቅመን ፈጣሪን ማመስገን እንችላለን ። ግእዝም እንደ ቋንቋ ፈጣሪያችን ልናመሰግንበት እንችላለን። ስለዚህ በዚህ ፅሁፍ ግእዝ እንደ ቋንቋ እንጂ ከሃይማኖት ጋር ምንም ትስስር እንደሌለው ኣስቀድሜ ለመግለፅ እውዳሎህ።**

ከዚህ በተጨማሪ የፊደሎቹ ኣጠቃቀምና እድገት በተመለከተ የተለያየ ኣስተያየት ሲሰጥ እሰማሎህ። ከሚሰጡ ኣስተያዬቶች መካከል ፣

- ትግርኛ የተበላሸ ኣማርኛ ነው የሚሉ ወገኖች ይደመጣሉ፣
- ኣሁን ለምንጠቀምባቸው ፊደሎች መነሻው ግእዝ ሁኖ ፣ ከግእዝ ደግሞ እንደ ኣማርኛ፣ ትግርኛ ሊወለዱ ችለዋል የሚሉም ኣሉ፣

- ግእዝን በመነሻነት ወስደው፣ ኣማርኛ ከትግርኛ ይቀድማል የሚሉ እንዳሉ ሁሉ ትግርኛ ይቀድማል የሚሉም ኣሉ ወዘተ።

ከላይ የተገለፀውን ኣስተያየት መሰረት በማድረግ፣ ኣንዳንድ ወገኖች ኣሁን የምንጠቀምበት ፊደል፣

- የኣማርኛ ፊደል ነው የሚሉ ኣሉ

  ወይም

- የግእዝ ፊደል ነው የሚሉ ኣሉ

  ወይም

- የትግርኛ ፊደል ነው የሚሉ ኣሉ

በእርግጥ የፊደለቹ መሰረት ከተጠቀሱት ሶስቱ ቋንቋዎች ኣንዱ ሊሆን እንደሚችል ኣስባሎህ ። በመሆኑም ለምን የኣማርኛ ፊደል ከሆነ በሌሎች ቋንቋዎች ፊደሉን እንጠቀምበታለን ለማለት ፈልጌ ግን ኣይደለም፣ ወይም በተገላቢጦሽ። ሆኖም ግን የላቲን ፊደል እንውሰድ። የላቲን ፊደል መሰረቱ ታውቆ በየትም ኣለም እየተጠቀምንበት እንገኛለን። ስለዚህ ኣሁን በኢትዮጵያ እየተጠቀምንበት ያለው ፊደል እንደ ላቲን ፊደል እውቅና ኣግኝቶ ጥቅም ላይ መዋል ያለበት ይመስለኛል።

በእርግጥ በተለያየ ወቅት የኣማርኛ፣/ የትግርኛ፣/ የግእዝ ፊደል ነው የሚሉ ክርክሮች በተለያየ ግዜ ይነሳሉ። ከሚነሱት መከራከርያ ሃሳቦች ኣንድ ነገር በኣእምሮዬ ጥልቅ ኣለ። እሱም ኣሁን የምንጠቀምበት ፊደል የድምፅ መስተጋብርና ይዘትን በተመለከተ ነው። በእርግጥ ሁላችንም እንደምናውቀው የፊደሎቹ የድምፅ መስተጋብርና ይዘት እንደምሳሌ ያገለግለኝ ዘንድ በሰንጠርዥ 1 ና 2 እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሰንጠረዥ 1: በ **ሀ** እና **ሐ** ዘሮች የድምፅ ተመሳሳይነትና ልዩነት በኣማርኛ፣ ትግርኛ ና ግእዝ ቋንቋዎች

| | ግእዝ/ኣንደኛ | ካእብ/ሁለተኛ | ሳልስ/ሶስተኛ | ራብእ/ኣራተኛ | ሃምስ/ኣምስተኛ | ሳድስ/ስድስተኛ | ሳብእ/ሰባተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መነፃፀርያ | ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| | ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| **በግእዝ ያለው ድምፅ** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** |
| **በኣማርኛ ያለው ድምፅ** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** | **ኣንድ ኣይነት ነው** |
| **በትግርኛ ያለው ድምፅ** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** |

ሰንጠረዥ 2: በ **አ** እና **ዐ** ዘሮች የድምፅ ተመሳሳይነትና ልዩነት በአማርኛ፣ ትግርኛ ና ግእዝ ቋንቋዎች

| | ግእዝ/አንደኛ | ካእብ/ሁለተኛ | ሳልስ/ሶስተኛ | ራብእ/አራተኛ | ሃምስ/አምስተኛ | ሳድስ/ስድስተኛ | ሳብእ/ሰባተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መነፃፀርያ | አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| | ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| **በግእዝ ያለው ድምፅ** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** |
| **በአማርኛ ያለው ድምፅ** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** | **አንድ አይነት ነው** |
| **በትግርኛ ያለው ድምፅ** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** | **የተለያዩ ነው** |

ከዚህ በተጨማሪ በእያንዳንዱ ሰንጠረዥ በግእዝ/አንደኛ እና በአራተኛ/ራብእ ዘለላ/columns/ያሉ ፊደሎች በተመለከተ በግእዝና በአማርኛ ቋንቋ አንድ አይነት ድምፅ ነው ያላቸው ። በትግርኛ ቋንቋ ግን ሁሉም ሆሄያት የተለያዩ ድምፅ ነው ያላቸው። ማለትም

- ሀ፣ሃ፣ሐ እና ሓ በአማርኛና በግእዝ አራቱም ሆሄያት አንድ ዓይነት ድምፅ ነው ያላቸው። በትግርኛ ቋንቋ ግን እያንዳንዱ ሆሄ የየራሱ የተለየ የድምፅ ውክልና ነው ያለው።
- አ፣ኣ፣ዐ እና ዓ በአማርኛና በግእዝ አራቱም ሆሄያት አንድ ዓይነት ድምፅ ነው ያላቸው። በትግርኛ ቋንቋ ግን እያንዳንዱ ሆሄ የየራሱ የተለየ የድምፅ ውክልና ነው ያለው ።

በእርግጥ ፊደል የሚቀረፀው ድምፅን ለመወከል ነው ብዬ አስባሎሁ ። በመሆኑም ፊደል የሚቀረፀው ለድምፅ ውክልና ነው በሚለው ሃሳብ እንስማማ። ከዚህ በመነሳትም አሁን የምንጠቀምበት ፊደል መጀመርያ ለግእዝ ወይም ለአማርኛ ልሳን/ድምፅ/ ነው የተቀረፀው ብለንም እንውሰድ። ፊደል ለድምፅ ውክልና የተቀረፀ ከሆነ፣

### ለምንድ ነው የተለያዩ ፊደሎች ለአንድ አይነት የሆነ የድምፅ ውክልና መቅረፅ ያስፈለገው?

ለዚህ ጥያቄ የተለያዩ መልስ ሊኖረን ይችላል ብዬ አስባሎሁ። ነገር ግን አንዳንዴ ሲነገር የሰማሁትን ለማንፀባረቅ እፈልጋሎሁ። አንዳንዶቹ አንድ አይነት ድምፅ ሁኖ የተለያዩ ፊደሎች ለተለያዩ ነገሮችን በውክልና እንደሚያገለግል ያስረግጣሉ።ለምሳሌ በአማርኛና በግእዝ

1. ኣ/ም እና ዓ/ም ኣግባብነት ያለው የሌለው ኣፃፃፍ ብለው ያስቀምጣሉ ፣

2. ፀሀይ ፀሃይ ፣ፀሓይ ፣ ፀሐይ፣ እንዲሁም ጸሀይ ፣ጸሃይ፣ ጸሐይ እና ጸሓይ እንመልከት፣ በአማርኛና በግእዝ ስድስቱ ቃላቶች ኣንድ ኣይነት ድምጽና መልእክት ያስተላልፋሉ። ነገር ግን ኣግባብነት ያለውና የሌለው ኣፃፃፍ ብለው ይፈርጁታል ወዘተ።

በተራ ቁጥር 1 እና 2 ያሉትን በሚያስተላልፈው ድምፅና መልእክት ያለው ልዩነት ሳይኖር በነገሮች ላይ የፊደል ኣጠቃቀማችን ኣግባብነት ያለውና የሌለው ኣፃፃፍ ብለው ይከራከራሉ። ኣግባብነትና ኣግባብ ያልሆነ የሚለውን ከወሰድን ደግሞ፣ ፊደሎች ከድምፅ ውክልና ባሽገር የነገሮችን ምልክት መሆናቸውን ያሳያል። በነገሮች የሚወከሉ ፊደሎችን መቅረፅ ደግሞ ለመግባባትም ሆነ ለማናጅመንት ያላቸው ኣስቸጋሪነት የሚያጠራጥር ኣይመስለኝም።

**በእርግጥ የኔ ዋና ኣላማ የተሟላና ወደ ድምዳሜ ሊያደርሰን የሚችል ጭብጥ ለማስያዝ ኣይደለም። ይልቁንስ በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎች ገሃዱን እንዲያወጡልን ለመጠየቅ ነው። ጥያቄዬ እንደተጠበቀ ሁኖ ግን ኣንድ ኣስተያዬት ለመስጠት እፈልጋሎህ።**

በኣለማችን በላቲን ፊደል የሚጠቀሙ ሰዎች/ኣገሮች የማህበረሰባቸውን የቋንቋ ድምፅ ለማካተት ያሙች ዘንድ በላቲን ፊደሎች/ሆሄያት ላይ የተለያዩ ቅጥያዎች ወይም ደግሞ በኣነባቢና ተነባቢ ሆህያት ላይ ድግግሞሽ ወይም ተጨማሪ ምልክቶች ያክላሉ። ይህ ሁኔታ የሚታይና የምጨበጥ እውነታ ነው። ስለዚህ ወደ ኣገራችን ሁኔታ እንውሰደውና መጀመርያ ፊደሎቹ በግእዝ/በኣማርኛ የተቀረፁ ናቸው ብለን እንውሰድ።

**እንዴት ነው በኣሁኑ ሰኣት ጥቅም ላይ ያሉ ፊደሎች ያለምንም ቅጥያ የትግርኛን ቋንቋ /ልሳን/ ሙሉ በሙሉ ገላጭ ሊሆኑ የሚችሉት? (በትግርኛ ከነኣካቴው የማንጠቀምባቸው ፊደሎች ሳይጨመር ማለት ነው)**

የዚህን ሙጉት በመነሻነት ከወሰድን ፊደሎቹ መጀመርያውኑ ለትግርና ቋንቋ ለማገልገል የተቀረፁ መሆናቸውን ያመላክታል ። ስለዚህ በስነ ፅሁፍ እምብዛም ያልዳበረው የትግርኛ ቋንቋ ላይ ጥልቅ ጥናት ማድረግና በኢትዮጵያችን ያለው የስልጣኔ ድርሻ ጎልቶ መውጣት ኣለበት እላሎህ ።